# ፍቅር እንደዚህ ነው

የቦታ ርቀት የማይገታው

የጊዜ ርዝመት የማይሽረው

ራስን የሚያሰጥ ስሌሳው

ከሳይ ወደታች ጎትቶ

የክብር ቦታን አስትቶ

ዙፋንን አስመንኖ

የሚያስተኛ ከጉረኖ

የማይወሰነውን አስወስኖ

የማይሆነውን አስሁኖ

በገዛ ራስ ወድዶ ፈቅዶ

ደካማና ብርቱ አዋሕዶ

ባሕርይ ከባሕርይ አዋድዶ

አንዱ አንዱን ሳያጠፋው

አንዱ ሌሳውን ሳይገዛው

ሳይለውጠው ሳይበርዘው

የአብ ክንዱን ቀኝ እጁን

የቅድምና ውድ ልጁን

በእጁ የሰራው አሳምሮ

ሕያው አድርጎ ባለ አእምሮ

በክፉ ምክር በጠሳት

መታለሉ አሳዝኖት

ከልቡ ገብቶ አገብሮት

በራሱ ጊዜ የሳበው

ያስጥፋቱ ያስቀጣው

በመስቀል ሳይ ያዋለው

እስከ መቃብር ያወረደው

እውነተኛው ፍቅር ደገኛው

ልብ እንበል እንደዚህ ነው።

ክፉ ክፉውን  አሰትቶ መልካም

መልካሙን የሚያሳይ

የማያስመካ የማያስታብይ

የማያቀናና የሚያስታግስ

የማያበሳጭ የሚያሰኝ ደስ

ይድሳኝ የማይል የሚያስተዛዝን

ስጠሳት ምሕረት የሚያስለምን

በሁሉ የሚጸና የሚያምን

የማያሳስብ ክፉ ነገር

ተስፋ የሚያደርግ የማይሻር

እውነተኛው ፍቅር ደገኛው

ልብ እንበል እንደዚህ ነው።


ደምስው ይነሱ

ኦስሎ